# አቻምየለህ

ኢትዮጵያችን በአገር ሻጭና ከእውቀት ነፃ በሆኑ ጥቅመኞች እጅ ወድቃ በተዛባ ትርክት በምትታመስበት በዚህ ወቅት ለእውነት የቆሙትን ሰዎች ማመስገን ግድ ይላል። ከነዚህም በርካታ የቁርጥ ቀን ልጆቿ መካከል ስምን መልዐክ ያወጣዋል እንዲሉ አቶ አቻምየለህ ታምሩ አንዱ ነው። አቻምየለህን ልዩ የሚያደርገው በየጊዜው ሀገርና ወገን ለማጥቃት ለሚነሱ የሀሰት ትርክቶች ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል የሀሰቱን ትርክት በማስረጃ እያስደገፈ በመፃፍና በማስረዳት ጎጠኞቹንና ጥቅመኞቹን እርቃናቸውን በማስቀረት አቅሙ ነው።

አቻምየለህ እንደልማዱ በርዩት ሚዲያ በቴዎድሮስ ፀጋየ አዋያይነት ልቡ ወደጎጠኞቹ ካደላው አናንያ ሶሪ ከተባለ የጭፍን ተሚጋች ጋር ቀርቦ ስለሀገር ባለቤትነትና ወረራ፣ ስለነፍጠኝነት ትርክት፣ ስለሀይማኖት፣ ቋንቋ፣ ስለጭቆናና መሬት ላራሹ፣ ስለተረኛው አስተዳደር ወ ዘ ተ የዛሬዎቹ የኦሮሞ ጎጠኛ ፓለቲከኞች ለመመረቂያ ያዘጋጁትን ፅሁፍ ሳይቀር በመረጃነት አቅርቦ ውይይቱን በድል አጠናቋል። የአቻምየለህን ፅሁፍ ማንበብና እሱ የሚለውን ማዳመጥ የቻለ ሰው ብዙ ሳይደከም ታሪኩን፣ ማንነትንና እውነትን ከእሱ ይማራል። በእውቀት የታጨቀው አቻምየለህ ታምሩ በፈጠራ ሳይሆን በእውነትና በማስረጃ ታሪክ እያጣቀሰ የሀሰት ትርክትን ለሚንደው፣ በትርክት ለተወናበደው ዜጋ እውቀት የማስጨበጥ ብቃቱ አድናቆቴን ለመቸር ይችን ስንኝ ቋጠርኩለት።



**አ-**ንሶ በሚያሳንስ፣ በተዛባ ትርክት፣ የሰው ልጅ ሲቀጠፍ

**ቻ-**ል አርጋው አገሬ፤ የሰቆቃውን ድምፅ፣ የህዝቧን የእምባ ጎርፍ

**ም-**ዝበራው ጥፋቱ፣ አሰቃቂው ወንጀል፣ ጭካኔው በርክቶ

**የ-**ሀሰቱን ትርክት፣ እርቃኑን የሚያስቀር፣ ያን ሁሉ ድሪቶ

**ለ-**ትውልድ ገላጭ፣ እውነት አፍረጥርጦ፣ ማስረጃ አሳይቶ

**ህ-**ዝብ አደናጋሪን፣ ጎጠኛውን ሁሉ፣ በታሪክ ሞግቶ

**ታ-**ሪክ አዋቂ ሰው፣ አቻምየለህ ብሎ፣ አምላኳ አስነስቶ

**ም-**ናምኑ ወሬ፣ ታሪክ እንዳልሆነ፣ በገሀድ አውጥቶ

**ሩ-**ቅ ያለመውን፣ የኢትዮጵያን ጠላት፣ አሸነፈ ረትቶ።

ውይይቱን መከታተል ለሚፈልግ https://www.youtube.com/watch?v=d9069Tt6uUk&t=1761s

ዘውዲቱ የማነ
2020-07-25